# ጥቅምት 15 ለምን የሠራዊት ቀን ሆኖ ይከበራል?

ኮሎኔል መስፍን ለገሠ ደበሌ[1]


## *አጽርኦት*

*ኢትዮጲያ የባለ ብዙ ታሪክ አገር ብትሆንም በታሪክ ደርሳናት አብዛኛውን ቦታ ይዞ የምናገኘው ግን የጦርነት ታሪክ ነው። ከነዚህ የጦርነት ታሪኮቻችን ውስጥ ኢትዮጲያን በተለያዩ ጊዜያት ሊወሩ ከመጡ ባዕዳን ወራሪዎች ጋር የተደረጉ ጦርነቶች በርካታ ናቸው።በነዚህ ሁሉ ጦርነቶች የኢትዮጲያ ሠራዊት ተጋድሎ አድርጎ፣ የአካልም የሕይወትም መስዋዕትነት ከፍሎላሬ ያለችውን ኢትዮጲያን አስረክቦን አልፏል። አሁንም በዚህ ዘመን ኢትዮጲያን እንደ አገር ለማቆየትና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሠራዊቱ አገሩና ወገኑ ከሱ የሚጠብቁትን በምንም የማይተመን መስዋዕትነት ያለስስት እየከፈለ ይገኛል። ሠራዊት እንዲህ አይነት መስዋዕትነት እንዲከፍል የጥንካሬው ምንጭ ሕዝብ ነውና፣ መስዋዕትነት የሚከፈልለት ሕዝብም ሠራዊቱን በተለያዩ ጉዳዮች በመደገፍ፣ ሞራልና ስነልቦናው ተጠብቆ እንዲቆይ በማበረታታት፣ ለሠራዊቱ ያለውን አለኝታነትና ጥልቅ ፍቅር ይገልፃል፣ ለሚከፍለው መስዋዕትነትም እውቅና ይሰጣል። ሠራዊት ለሚከፍለው መስዋዕትነት ዘወትር ክብር መስጠት ተገቢ ቢሆንም የተለያዩ መነሻዎችን መሰረት አድርጎ ከዓመቱ ቀናት አንዱን የሠራዊት ቀን አድርጎ በብሔራዊ ደረጃ ማክበር በዓለማችን በበርካታ አገራት የተለመደ አሰራር ነው። የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴርም ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጲያ መከላከያ ሠራዊት ቀን በየዓመቱ ጥቅምት 15 ቀን እንዲከበር ወስኗል። በመሆኑም ይህ አጭር ጽሁፍ የሠራዊት ቀንን አስፈላጊነትና በተለይ የሠራዊት ቀን አመራረጥን በተመለከተ የተወሰኑ የውጭ አገራት ተሞክሮዎችን በአጭሩ በመዳሰስ፣ ከአገራችን ታሪክ ውስጥ ደግሞ ለሠራዊት ቀን ሊሆኑ የሚችሉ ታሪካዊ ኩነቶችን ቃኝቶ ጥቅምት 15 የሠራዊት ቀን ሆኖ እንዲከበር የተወሰነበትን መነሻ የሚያቀርብ ይሆናል።*


**ቁልፍ ቃላት:** የሠራዊት ቀን፣ የኢትዮጲያ መከላከያ ሠራዊት፣ ጥቅምት 15፣ ታሪክ

## 1 የሠራዊት ቀን አስፈላጊነት

ሠራዊት ከህዝብ የሚወጣ የአገር ዋልታ ነው። ሠራዊት ህዝብን በሚያገለግል መንግስት እየተመራ የህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ፣ ህዝብ ህይወቱን በሰላም እንዲመራ፣ በሰላም ሰርቶ እንዲኖር፣ ኃብት እንዲያፈራ፣ ቤተሰብ እንዲመሰርት፣ ባጠቃላይ የህይወት ህልሙን እውን እንዲያደርግ እሱ የህይወት መስዋዕትነት የሚከፍል፣ እሱ እንደህዝብ እነዚህ ፍላጎቶችና የህይወት ህልም ቢኖረውም ለሌሎች ህልም መሳካት የራሱን ህልም አሳልፎ የሚሰጥ፣ ባጠቃላይ ለአገሩና ለወገኖቹ ሰላምና ደህንነት መተኪያ በሌላት ህይወቱ ያለምንም ማመንታት መስዋዕት የሚሆን የህዝብና የአገር ብሔራዊ ኩራት ነው።

ሠራዊት በዚህ ተግባሩ በተያዩ አገራት በተለያየ ሁኔታ በህዝብ ዘንድ በታላቅ ክበሬታ እንደሚታይ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ሰምተን ይሆናል፣ አንብበን ወይም በአይናችን አይተን ይሆናል። ለምሳሌ በአሜሪካ አገር ወታደራዊ የደንብ ልብስ ለብሶ አውሮፕላን ለመሳፈር የተገኘ የሠራዊት አባል ቀድሞ ወደአውሮፕላኑ ሳይገባ ሌላው ተሳፋሪ እንደማይገባ፣ በተለያዩ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ቅድሚያ እንደሚሰጠው፣ በሌሎች አገራት በተለያዩ መንገዶች ለሠራዊት የሚሰጡ የአክብሮት ተግባራትን አይተን ወይ ሰምተን ይሆናል። የነዚህ አክብሮቶች መነሻ ሠራዊቱ ከሚወጣው ተልዕኮና ከሚከፍለው መስዋዕትነት የሚመነጩ ናቸው። እንደዚህአይነት ክብር የሚሰጠውና ለሚከፍለው የተከበረ መስዋዕትነት ህዝብ ድጋፍና ፍቅር የሚቸረው ሠራዊት ለህዝብ ጥቅም ራሱን አሳልፎ ለመስጠት ፈፅሞ የማያመነታ፣ ጠንካራ እና ድል አድራጊ ሠራዊት ይሆናል። ለዚህ ነው የመከላከያ ሠራዊታችን የጥንካሬ፣ ወይም የድል አድራጊነት ምንጭ ህዝብ ነው የምንለው።

በመሆኑም ሠራዊት ለሚከፍለው መስዋዕነት መስዋዕትነት የሚከፈልለት ሕዝብ ሠራዊቱን በተለያዩ ጉዳዮች ዘወትር መደገፍ፣ ሞራልና ስነልቦናው ተጠብቆ እንዲቆይ ማበረታታት፣ ለሠራዊቱ ያለውን ክብር በተለያዩ አጋጣሚዎች መግለጽና ለሚከፍለው መስዋዕትነትም እውቅና መስጠት መልካም ፈቃደኝነትን የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን ሞራላዊ ግዴታም ነው። በተመሳሳይ ሠራዊቱም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለህዝቡ ያለውን ታማኝነት ሊገልፅና ለህዝብ ጥቅም ህይወቱን አሳልፎ ሊሰጥ የገባውን ቃልኪዳን ዳግም ሊያድስ የሚችልበት መድረክ ያስፈልገዋል። በመሆኑም የሠራዊት ቀን ህዝቡ ለሠራዊቱ ሠራዊቱም ለህዝቡ ያለውን ክብርና ታማኝነት በተለያዩ መንገዶች የሚገልፁበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል።

## 2 የሠራዊት ቀን አመራረጥ በተለያዩ አገራት

የሠራዊት ቀን የሚከበርበትን ቀን አገራት የተለያዩ መነሻ ምክንያቶችን መሰረት አድርገው ይወስናሉ። እነዚህን መነሻ

[1] ኮ/ል (ጡ) መስፍን ለገሠ በኢፌዲሪ መከላከያ የጥናትና ምርምር ማዕከል ባልደረባ የነበሩ፤ mesfinlegese@gmail.com

ምክንያቶች በመሰረታዊነት በሶስት ክፍለን ማየት እንችላለን። ይኸውም የመከላከያ ሠራዊቱ በይፋ የተቋቋመበት ቀን፣ ወይም በአገራቸው የተካሄደ በተለይም የአገራቸውን ነፃነት ለማረጋገጥ የተደረገ ውጊያ ወይም ጦርነትን እንዲሁም ሠራዊታቸው በቅኝ ገዢዎች ከመመራት የተላቀቀበትን ቀን በማሰብ የሚደረጉ ናቸው።

## 2.1 ሠራዊታቸው የተመሰረተበትን ቀን የሚያከብሩ አገራት

ሠራዊታቸው የተመሰረተበትን ቀን ከሚያከብሩ አገራት አንዷ ቻይና ነች። እ.ኤ.አ. ኦገስት 1 ቀን የሚከበረው የቻይና ህዝባዊ ነፃ አውጪ ሠራዊት (People's Liberation Army) ቀን የቻይና ህዝባዊ ነፃ አውጪ ሠራዊት የተመሰረተበትን ቀን ለማሰብ ነው[2]። ፊሊፒንስም እንደቻይና የጦር ሠራዊቷ በ1935 ዓ.ም በህግ የተመሰረተበትን ዲሴምበር 21 ቀን የሠራዊት ቀን አድርጋ ታከብራለች[3]።በተመሳሳይ ቬይትናም ዲሴምበር 22 1944፣ ሩሲያ ፌብሩዋሪ 23 1918፣ ሰሜን ኮርያ አፕሪል 25፣ እንዲሁም አርሜንያ፣ ጆርጂያ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ጃፓን፣ ኢራቅ፣ ካዛክስታን፣ ላኦስ፣ ማሌዥያ፣ ቦሊቪያ እና ሜክሲኮን ጨምሮ በርካታ አገራት ሠራዊታቸው የተመሰረተበትን ቀን ምክንያት አድርገው የሠራዊት ቀንን ያከብራሉ።

በአሜሪካ የሠራዊት ቀን ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ እ.ኤ.አ. በየዓመቱ በሜይ ወር ሶስተኛው ቅዳሜ ላይ የሚከበር ሲሆን ቀኑ የሚከበረውም በአምስቱ የአሜሪካ የጦር ኃይል ክፍሎች ማለትም በምድር ኃይል፣ በባህር ኃይል፣ በማሪን ኮር፣ በአየር ኃይል እና በጠረፍ ጥበቃ ኃይሉ በማገልገል ላይ ያሉ የሠራዊት አባላትን ለማሰብ ነው[4]። በዓሉ በዚህ ቀን መከበር የጀመረበት ዓላማም አምስቱ የሠራዊቱ ክፍሎች በአሜሪካ የመከላከያ መስሪያ ቤት (Department of Defense) በአንድ አስተዳደር ከተዋሃዱ በኋላ ክፍሎቹበግል የሚያከብሩትን ቀን ለማስቀረት ታስቦ ነው። በርግጥ ይህም ሆኖ ክፍሎቹ ግን አሁንም የራሳቸውን ቀን በተናጠል ማክበር አላቆሙም።

## 2.2 የሠራዊታቸው አመራር ከቅኝ ገዢዎች የተላቀቀበትን ቀን የሚያከብሩ አገራት

በቅኝ ገዢዎችሲመራ የነበረውን ሠራዊታቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ በራሳቸው ዜጎች መምራት የጀመሩበትን ጊዜ የሠራዊት ቀን አድርገው ከሚያከብሩ አገራት አንዷ ህንድ ናት። ህንድ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 15 ቀን 1949 የህንዱ ፊልድ ማርሻል ኮዳንዴራ (Kodandera) የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ከነበረው እንግሊዛዊው ጄነራል ፍራንሲስ በቸር (Francis Bucher) የአዛዥነት ስልጣኑን የተረከበበትን ቀን የሠራዊት ቀን አድርጋ ታከብራለች[5]። ደቡብ አፍሪካ አገሪቱ ከአፓርታይድ አገዛዝ ተላቃ የደቡብ አፍሪካ ሠራዊት አሁን ባለው መልኩ አገራዊ ሠራዊት ሆኖ የተዋቀረበትን ፌብሩዋሪ 21 ቀን 1993 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) ምክንያት አድርጋ የሠራዊት ቀንን ታከብራለች[6]። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከ2007 ጀምሮ የሠራዊት ቀን በ1ኛው የዓለም ጦርነት በ1917 SS Mendi የተሰኘችው የደቡብ አፍሪካ መርከብ ወታደሮችን አሳፍራ ወደ ጦርነቱ ስትጓዝ የሰመጠችበትንና በደቡብ አፍሪካ ሠራዊት ታሪክ ከፍተኛ የተባለው ኪሳራ የደረሰበትን ቀን በማሰብም እንዲከበር ተደርጓል።

## 3.3 በአገራቸው የተካሄደ ቁልፍ ውጊያ ወይም ጦርነትን ለማሰብ የሚያከብሩ አገራት

በሁለተኛ ደረጃ የምናየው በአገራቸው የተካሄደ ቁልፍ ጦርነትን ለሠራዊት ቀን መነሻ አድርገው የሚወስዱ አገራትን ነው። ከነዚህ ውስጥም ባንግላዴሽ፣ ግብፅና በርካታ የአውሮፓ አገራት ይገኙበታል። ባንግላዴሽ የጦር ኃይሎች ቀን የምታከብረው ከፓኪስታን ኃይሎች ነፃ ለመውጣትየባንግላዴሽ ሶስቱም ኃይሎች እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 21 ቀን 1971 ዓ.ም ያካሄዱትን የህብረት ዘመቻ ለማሰብ ነው። ግብፅ የጥቅምት ጦርነት በመባል በሚታወቀውና በ1973 በተካሄደው ጦርነት ከሶርያ ሠራዊት ጋር በመቀናጀት ሲናይ ሰላጤን ተሻግራ በእስራኤል ላይ ድንገተኛ ጥቃት የሰነዘረችበት የYom Kippur ጦርነት

---

[2] ZD. China Focus: "Be ready to win wars," China's Xi orders reshaped PLA. Xinhua. 01, August 2017. http://www.xinhuanet.com// english/2017-08/01/c_136491455.htm, Accessed on 03 September 2023.

[3] PAGASA. "The 80th Armed Forces of the Philippines Day". Official Gezette. 21 December. 2015. https://www.officialgazette .gov.ph/2015/12/21/the-80th-afp-day/, Accessed on 01 September 2023.

[4] U.S. Government Publishing Office "Armed Forces Day". 12, May 2020. https://www.govinfo.gov/features/armed-forces-day. Accessed on 01 September 2023.

[5] Ministry of Defense. "Indian Army celebrated its 74th Army Day". PIB Delhi. 15, January 2022. https://pib.gov.in/ PressReleasePage. aspx?PRID=1790154, Accessed on 01 September 2023.

[6] Department of Military Veterans. "President Jacob Zuma presides over Armed Forces Day celebration in Port Elizabeth, 21 Febraury". 04, February 2016. http://www.dmv.gov.za/news/armed-forces-day.htm, Accessed on 29, August 2023.

የተጀመረበትን ኦክቶበር 6 ቀን የጦር ኃይሎች ቀን አድርጋ ታከብራለች[7]። ናይጀሪያ በተመሳሳይ በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዲሁም ከቢያፍራን (Biafran) ኃይሎችን ጋር በነበረ የእርስበርስ ጦርነት (Civil War) መስዋዕትነት የከፈሉ የናይጀሪያ ጦርኃይል አባላትን ለማሰብ ጁላይ 6 በሚጠናቀቅ የአንድ ሳምንት ፕሮግራም የጦር ኃይሎች ቀን ይከበራል[8]። ወደጣሊያን ስንሄድ ደግሞ የጣሊያን የጦር ኃይሎች ቀን የሚከበረው በአንደኛው የዓለም ጦርነት በኦስትሪያ ሃንጋሪ ግንባር ኖቬምበር 4 1918 ዓ.ም በኢጣሊያ አሸናፊነት የኦስትሪያ ሃንጋሪ ሠራዊት ተኩስ ለማቆም ስምምነት ላይ የደረሰበትን ቀን ምክንያት በማድረግ ነው[9]። ፖላንድም በተመሳሳይ በ1920 በተካሄደው የዋርሶ ውጊያ በሶቭየት ሠራዊት ላይ ድል የተቀዳጀችበትን ቀን[10]፣ ሮማኒያ ደግሞ የመጨረሻውን ግዛቷን ከጀርመን እና ሃንጋሪ የህብረት ኃይሎች ያስመለሰችበትን ኦክቶበር 25 1944[11] ምክንያት በማድረግ የሠራዊት ቀን ታከብራለች።

ባጠቃላይ ሲታይ የሠራዊት ቀን በአብዛኛው ሠራዊቱ የተመሰረተበት ወይም በይፋ ስራ የጀመረበት ቀን፣ ወይም የተለያዩ ኃይሎችን ባንድ ላይ ተጣምረው ህጋዊና አገራዊ ተቋም የፈጠሩበት ቀን፣ በአንዳንዶች አገላለፅ የሠራዊቱ Birthday ተደርጎ ይቆጠራል።

## 3. የአገራችን የሠራዊት ቀን ተሞክሮ

ከሠራዊት ቀን አከባበር ጋር በተያያዘ ወደ አገራችን ተሞክሮ ስንመጣ፣ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በፊት የሠራዊት ቀን ባይኖርም የአድዋ በዓልን፣ የነገሥታት የልደት ቀንን ወይም የንግስና በዓልን ለማክበር ሠራዊቱ የሰልፍ ትርኢት የሚያደርግባቸው ጊዜያት ነበሩ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ከ1948 ዓ.ም ጀምሮ በምድር ኃይሉ የተለያዩ ክፍሎች መሃልዓመታዊ የስፖርት ቀን ግንቦት ወር ላይ ይካሄድ ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግንቦት 20 ቀን 1950 ዓ.ም ሁሉንም ኃይሎች ያካተተውን የመጀመሪያውን የጦር ኃይሎች የስፖርት ውድድር ንጉሠ ነገሥቱ እንዲታደሙ ተደርጎ ነበር[12]። ንጉሱም ውድድሩ በሠራዊታቸው ውስጥ የፈጠረው መነቃቃት አስደስቷቸው ዕለቱ የጦር ኃይሎች ቀን ሆኖ በየሶስት ዓመቱ እንዲከበር ውሳኔ አስተላልፈዋል። በውሳኔያቸው መሰረትም የጦር ኃይሎች ቀን በየሶስት ዓመቱ ለአንድ ሳምንት በተለያዩ የስፖርት ውድድሮች ሲከበር ቆይቷል። ከ1966 በኋላ የጦር ኃይሎች ቀን አንዴ ሲከበር አንዴ ሲቋረጥ ቆይቷል። ከ1987 ዓ.ም ጀምሮም የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በአዋጅ የተቋቋመበትን ቀን ለማሰብ የካቲት 7 ቀን የሠራዊት ቀን ሆኖ ሲከበር መቆየቱ ይታወሳል።

በአገራችን የተለያዩ የአገዛዝ ዘመናት የሠራዊት ቀን ቋሚ በሆነ መልኩም ባይሆን ለማክበር የተደረጉ ሙከራዎች ቢኖሩም የኢትዮጲያ መከላከያ ሠራዊት ቀን ዓለም የመሰከረለትንና የረጂም ጊዜ ታሪክ ያለውን የኢትዮጲያንና የኢትዮጲያ ሠራዊትን ታሪክ ያገናዘበና ኢትዮጲያን የሚመጥን ሊሆን እንደሚገባ ይታመናል። ይህንንም በማድረግ ሠራዊቱና የሠራዊቱ ታሪክ ከመጣው ጋር አብሮ የሚቀያየር ሳይሆን ዘመን ተሻጋሪ፣ ታሪኩም ቀጣይ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። ለአገር ሉዓላዊነትና ለህዝቦች ነፃነት መከበር የተደረጉ በርካታ የጦርነት ታሪኮች አሉን። በሌላ በኩል ደግሞ ሠራዊታችን ዛሬ እዚህ እንዲደርስ መሰረት የጣሉና በተለያዩ የአገራችን መንግስታት የተከናወኑ የተለያዩ ዋረቶችም አሉ። በመሆኑም እነዚህ ታሪካዊ ኩነቶች ተዳሰው የትኛውን ቀን የሠራዊት ቀን ሊሆን ይገባል የሚል ኃሳብ ቀርቦ ከታየ በኋላ፣ ሁሉም የየራሳቸው ፋይዳ ቢኖራቸውም፣ በተለያዩ መመዘኛዎች ጥቅምት 15 ቀን የሠራዊት ቀን ሆኖ እንዲከበር ተወስኗል።

ጥቅምት 15 ቀን የሠራዊት ቀን ሆኖ ሲመረጥ ምን ምን ታሪካዊ ኩነቶች ነበሩ የተዳሰሱት የሚለውን የተወሰኑ አገራዊ

---

[7] National Today. "Egypt: Armed Forces Day – October 06, 2023". 06, October 2023. https://nationaltoday.com/egypt-armed-forces-day/, Accessed on 08 October 2023.

[8] Beshir Ahmed. "Armed Forces Remembrance Day 2022 highlight: January 15 in Nigeria history – Explainer". 15, January 2022. BBC News. https://www.bbc.com/pidgin/media-60009354, Accessed on 08, September 2023.

[9] Paolo Melissi. "4 November: Italian Unity and Armed Forces Day". Italian Traditions. 04, November 2022. https://italian-traditions.com/4-november-italian-unity-armed-forces-day/, Accessed on 02, September 2023.

[10] Ministry of National Defense. "Polish Army Day 2022". 27, July 2022. https://www.gov.pl/web/national-defence/polish-army-day-2022, Accessed on 02, September 2023.

[11] Embassy of Romania in Bosnia and Herzegovina. "25 October - Romanian Armed Forces Day", https://sarajevo.mae.ro/en/local-news/862, Accessed on 02, September 2023.

[12] ገስጥ ተጫኔ፣ የቀድሞው ጦር - 1927-1983፣ አዲስ አበባ፣ ዜድ.ኤ. ማተሚያ ቤት፣ 2006፣ 559።

ታሪካዊ ኩነቶችን መሰረት በማድረግ በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፣

## 4. ለሠራዊት ቀን የተዳሰሱ ዋና ዋና ታሪካዊ ኩነቶች

### 4.1 የአፄ ቴዎድሮስ ብሔራዊ ሠራዊት የማቋቋም ፍላጎት

አገራዊ ሠራዊት ከመመስረት አንፃር ቀዳሚው ኃሳብና ፍላጎት ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል። ቴዎድሮስ በንግስናቸው ዘመን በአንድ ዕዝ የሚተዳደር ብሄራዊ ሠራዊት እንዲኖር ባላቸው ፍላጎት "ወታደር የንጉሰ ነገስቱ እንጂ እንደቀድሞው የራሶችና የደጃዝማቾች የግል ጦር አይደለም። ራስም ሆነ ደጃዝማች የወታደር ዓለቃ እንጂ አሳዳሪ አይሆንም። የወታደር አሳዳሪ ንጉሰ ነገስቱ ብቻ ነው።" በማለት የሠራዊታቸውን አስተዳደርና ዕዝለማማከል ታጥቀው ተነስተው ነበር። ሠራዊታቸው ዘመናዊ አሰራር እንዲከተልም ዓለቃና ምንዝሩ የሚታወቅበት የማዕረግ መጠሪያም እንዲኖር አድርገዋል። ከማዕረግ አንፃር የማዕረግ ምልክት ባይኖርም ራስ፣ ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ሊቀመኳስ፣ ባላምባራስ፣ የሺአለቃ፣ ባሻ እና የሃምሳ ዓለቃ ማዕረጎችን ሰጥተዋል። በወቅቱ ለአገራዊ ሠራዊት ምስረታ ዋናው አሳሳቢ ጉዳይ ቀለብ ወይም ደመወዝ ስለነበር ከቤተክርስቲያን ርስት ቀንሰው ለሠራዊታቸው ቀለብ ወይም ደመወዝ ለመስጠት ቢወስኑም ከቀሳውስቱ ከፍተኛ ተቃውሞ ስለገጠማቸው ሃሳባቸው እንደፈለጉት እውን ሳይሆን ቀርቷል።

ደጃዝማች ካሣ ወይም ዮሐንስ አራተኛም እንደ አፄ ቴዎድሮስ ሁሉ እርሳቸውም ሠራዊታቸውን ከገበሬው ጥገኝነት ለማላቀቅ ባይችሉም በራስ አሉላ የሚመራ ዘመናዊ ትጥቅ የታጠቀማዕከላዊ ሠራዊት ለማደራጀት ጥረት አድርገዋል።

### 4.2 የአድዋ ጦርነት - የካቲት 23 1888

የካቲት 23 ቀን 1888 ተካሂዶ በዚያው ቀን የተጠናቀቀው የአድዋ ጦርነትና የተገኘው ድል የኢትዮጲያ ብሔራዊ ክብር ማኅተም በመሆን የአገራችንን ነፃነት አስከብሮ ያቆየ ከመሆኑም በላይ የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ ቀንዲል ሊሆን የበቃ ታላቅ ታሪካዊ ኩነት ነው። ጦርነቱ በተጀመረ ከአምስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሃምሣ ስድስቱም የኢጣሊያ መድፎች ሙሉ ለሙሉ ተማርከዋል፤ የቅኝ ገዢውን ወራሪ ሠራዊት ከመሩት ጀኔራሎች መካከል ጄኔራል አልቤርቶኒ ሲማረክ የሠራዊቱ ዋና አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ከጥቂት አጃቢዎቹና በሽንፈት ከተበታተኑ የኢጣሊያ ወታደሮች ጋር ሸሽቷል[13]።

በዚህ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ከኃምሳ ስድስቱ የኢጣሊያ መድፎች በተጨማሪ ብዙ ሺህ ቀላልና ከባድ መትረየሶች እንዲሁም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መሰል ጥይቶቻቸው ጋር ተማርከዋል። በአጠቃላይ ምርኮው ወደ አዲስ አበባ የተጓጓዘው በአምስት መቶ አጋሰሶች ተጭኖ እንደነበር ይነገራል[14]።

ይህ ታላቅ ድል የኢትዮጲያ ብቻ ሳይሆን የጥቁር ህዝቦች ድል በመሆን በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል። የእንግሊዝ ጋዜጦች በአድዋ ድል ማግስት የዓለም ታሪክ ተገለበጠ ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪቃ ተቀሰቀሰ ... ብለው የፃፉለት ድል ነው።

### 4.3 የጦር ሚኒስትር መቋቋም[15]

ከአድዋ ድል በኋላ ዳግማዊ አጤ ምኒሊክ ዘመኑ ያፈራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጲያ እንዲገቡ ከማድረጋቸው ጎን የመንግስት አመራራቸውም ዘመናዊ እንዲሆን በመሻታቸው ጥቅምት 15 ቀን 1900 ዓ.ም[16] በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በየስራ ዘርፉ ሚኒስትሮችን ሾመዋል[17]። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በአዋጅ የተቋቋመውና በፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ የሚመራው የጦር ሚኒስቴር ነበር[18]። በአዋጁ መሰረትም "የጦር ሚኒስቴር የንጉሠ ነገሥት ሠራዊት አለቃ ነው፣ ወታደር በጭፍራው እንዲቀመጥ፣ ሠራዊት ሁሉ የጦር ትምህርት እንዲማር ይጠብቃል"[19] በሚል ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

የጦር ሚኒስቴርን ያቋቋመው አዋጅ የወደፊቱ የኢትዮጲያ ሠራዊት ዘመኑ በሚጠይቀው መንገድ መደራጀት እንደሚገባው

---

[13]ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጲያ ታሪክ - ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ አዲስ አበባ፣ 1936፣ 97።

[14] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጲያ አንድነት፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983፣ 423።

[15] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጲያ ታሪክ - ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ 121።

[16] ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ዝክረ ነገር፣ አዲስ አበባ፣ ነፃነት ማተሚያ ቤት፣ 1942፣ 59።

[17] Paul B. Henze, Layers of Time – A History of Ethiopia. London: Palgrave. 2002,186.

[18] መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ- የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1999፣ 49።

[19] ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ዝክረ ነገር፣ 228።

ጠቋሚ ነበር። አዋጁ ሠራዊቱ በንጉሠ ነገሥቱ እንዲሁም ከርሳቸው በታች ባሉ ራሶችና ደጃዝማቾች የሚሰጥ የማዕረግ ሥርዓት-ደንብ ነበረው። ማዕረጉ የቀድሞ ነገሥታት ለጦር አበጋዞቻቸውና በተዋረድ ለሚገኙ ተዋጊዎች ይሾሙት የነበረውን መሰረት ያደረገ ነበር። የማዕረጉ ደረጃና ምንነት የሚገለፀውም ሹሙ በሚለብሰው፣ በራሱ ላይ በሚያደርገው፣ በሚይዘው ጋሻና በሚታጠቀው ጎራዴ ላይ በሚታየው ጌጥ እንዲሁም ጌጡ በተሰራበት ቁስ ነበር።

በዳግማዊ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት የሠራዊት ቀን ባይኖርም በአድዋ ድል በዓል፣ በንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ መታሰቢያና በመስቀል በዓል ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ጨምሮ ሠራዊቱ በሰልፍ እንዲያልፍ ይደረግ ነበር። በዚህ ሁኔታ የነበረው የምኒሊክ ሠራዊት ታህሳስ 3 ቀን 1906 ዓ.ምእርሳቸው ሲሞቱ እንደሌላው ጊዜ ሠራዊቱ ሳይበተን ባለበት ፀንቶ ዙፋኑን ለወረሱት ለልጅ እያሱ ማገልገሉን ቀጥሏል። ይህ ሁኔታ የኢትዮጲያ ህዝብ በአንድ መንግሥት ሥር መርጋቱንና ሠራዊቱን ይመሩ የነበሩት መሣፍንትና መኳንንት የንጉሠ ነገሥቱን የጦር ኃይሉ ጠቅላይ አዛዥነት መቀበላቸውንያመላክተ ነበር።

## 4.4 የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ/የክብር ዘበኛ መቋቋም

ከአፄ ምኒሊክ የጦር ሚኒስቴር ማቋቋም በኋላ በኢትዮጲያ ቋሚና ዘመናዊ ጦር የማደራጀት ሕልም እውን ለማድረግ መሰረታዊ እርምጃ ተወስዷል ሊባል የሚችለው አፄ ኃይለ ሥላሴ የክብር ዘበኛ ጦርንለማቋቋም በ1910 ዓ.ም የወሰዱት እርምጃ ነው። ይህ እርምጃ የአንድን ወታደር አካላዊና አዕምሯዊ ብቃት በዘመናዊ የውጊያ ዘዴና ወታደራዊ ሥነ ሥርዓት በማነፅ፣ ዘመናዊ መሳሪያ በማስታጠቅና ባጠቃላይ አንድ ወጥ አስተምህሮ /ዶክትሪን/ እና አንድ ዕዝ ያለው መደበኛ ሠራዊት የመፍጠር ጭላንጭል የታየበት ነበር። የክብር ዘበኛ ሠራዊት በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜም ከ1914 ጀምሮቀለብ በየወሩ የሚሰፈርለትና ዓመታዊ ደመወዝም እንዲከፈለው ተደርጎ ነበር።

ከዚህም በተጨማሪ በ1920 ዓ.ም ስድስት የውጊያ አውሮፕላኖችን ጨምሮ 11 የተለያዩ አገልግሎት ያላቸው አውሮፕላኖች ወደአገር ቤት ገብተው የአየር ኃይል ጥንስስም የተጀመረበት ሁኔታ ነበር። ከዘመናዊ ውትድርና ስልጠና ጋር በተያያዘም በስዊድን ድጋፍ የሆለታ የጦር መኮንኖች ትምህርት ቤት ጥር 21 ቀን 1927 ዓ.ም ባጠቃላይ 128 ዕጩ መኮንኖችን ተቀብሎ ስልጠና እንዲጀምርተደርጓል።

## 4.5 መጋቢት 28/ሚያዚያ 27 1933 ዓ.ም

የኢጣሊያ መንግስት በ1888 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት የደረሰበትን ታላቅ ውርደትና ኪሳራ ለመበቀል ከ40 አመት በኋላ በ1928 ዓ.ም በአገራችን ላይ ዳግም ወረራ ፈፀመ። ኢትዮጲያውያን አርበኞች ለተከታታይ አምስት አመታት ወራሪውን በዱር በገደል ሲፋለሙ ቆይተው መጋቢት 28 ቀን በ1933 ዓ.ም አዲስ አበባ የገቡት አርበኞች በዳግማዊ ምኒሊክ ቤተመንግስት ላይ የኢትዮጲያን ባንዲራ ዳግም አውለብልበዋል።[20] ይህን ተከትሎም ከአንድ ወር በኋላ ሚያዚያ 27 ቀን ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ የገቡ ሲሆን ዕለቱም የድል ቀን ሆኖ ሊከበር በቅቷል።

## 4.6 የጦር ሚኒስትር ህገመንግስትን መሰረት ባደረገ ደንብ በዘመናዊ መልክ ስራ የጀመረበት - ታሕሳስ 15 1944 ዓ.ም

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግስት እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ስራ ላይ የዋለና ከምክትል አስር አለቃ እስከ ማርሻል ድረስ ያለውን ወታደራዊ ማዕረግ ያካተተ የማዕረግ ምልክትና የደንብ ልብስ ወይም ዩኒፎርም እንዲለበስ ታህሳስ 15 ቀን 1944 ዓ.ም የወቅቱን ህገመንግስት ቁጥር 11 መሰረት አድርጎ በወጣ ደንብ ተደንግጓል[21]። ከዚህ በፊት በሠራዊቱ ከእንግሊዝ አሰልጣኞች የተወረሰ የማዕረግ ምልክት ጥቅም ላይ ውሎ እንደነበር ይነገራል። በዚሁ ዓመት ጥር 1 ቀን ስለጦር ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የአደረጃጀት ተዋረድ ጨምሮ በርካታ ጉዳዮችን ያካተተ የጦር ሚኒስቴር አቋምና የውስጥ ደንብ ወጥቶ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ከዚህ በኋላም በ1946 ዓ.ም በቁጥር 11/1946 አዋጅ መሰረት የአየር ኃይልና ባህር ኃይል ተመስርተው የራሳቸው በጀት ተመድቦላቸው በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ስር እንዲዋቀሩ ተደንግጓል። ይህንንም መሰረት አድርጎ በግንቦት ወር 1947 የጦር ሚኒስቴር ሶስቱንም ኃይሎች በአንድነት በማስተባበር የአገር መከላከያ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲቋቋም ተደርጓል።[22] ንጉሡ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፣ የጦር ሚኒስትር የነበሩት ሌ/ጀኔራል አበበ አረጋይ የአገር መከላከያ ሚኒስትር፣ እንዲሁም ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ሜ/ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ነበሩ። ከዚህም በተጨማሪ በ1950 ዓ.ም ንጉሡ ሰብሳቢ፣ አልጋ ወራሹ ምክትል ሰብሳቢ፣ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ፣ የውጭ ጉዳይ

---

[20] ገስጥ ተጫኔ፣ የቀድሞው ጦር - 1927-1983፣ 96።

[21] ገስጥ ተጫኔ፣ የቀድሞው ጦር - 1927-1983፣ 173።

[22] አበበ ወ/ተንሳይ፣ ቀ.ሥ ና ጦር ሥ. አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ቤት፣ 2000፣ 29።

ሚኒስትሩና የአገር ግዛት ሚኒስትሩ አባል የሆኑበት የአገር መከላከያ የምክር ጉባኤ ተቋቁሟል።

## 4.7 የሶማሌ ወረራ መቀልበስ - ጥር 26 1970 ዓ.ም

የአገርን ሉዓላዊነት ከማስከበር አንፃር የተደረገ ጦርነትን እንደአንድ መነሻ በመውሰድ ምናልባትም ከአድዋ ቀጥሎ የሶማሊያ ጦርነት ሊነሳ ይችላል። የሶማሊያ ወረራ ሰኔ 25 1969 ዓ.ም በኦጋዴን አውራጃ ዶሎን በመያዝ የተጀመረ ነበር። የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት በታጠቀው ዘመናዊ መሳሪያና የሠራዊት ብዛት በአካባቢው በነበረ አነስተኛ የኢትዮጲያ ሠራዊት ላይ ባረጋገጠው የውጊያ የበላይነት የምስራቅ ኢትዮጲያን በርካታ ስፍራዎች ለመያዝ ችሎ ነበር። ይሁን እንጂ በአጭር ጊዜ ውስጥበተደረገ ዝግጅት ወሳኝ የሆነ የመልሶ ማጥቃት ውጊያው ተካሂዶ ጥር 26 ቀን 1970 ዓ.ም በወረራ የተያዙ መሬቶች ሁሉ ነፃ ወጥተው የመልሶ ማጥቃት ውጊያው በድል ተጠናቋል። የሶማሊያ ጦርነት የአገራችንን ሉአላዊነት ከማስከበር አንፃር ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው ነው።

## 4.8 የካቲት 7 ቀን 1988 ዓ.ም

ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በአዋጅ የተቋቋመበትን ቀን ምክንያት በማድረግ የካቲት 7 ቀን የመከላከያ ሠራዊት ቀን ሆኖ ሲከበር መቆየቱ ይታወሳል።

## 5. ከላይ በቀረቡት ታሪካዊ ቀናቶች ላይ የቀረበ አጭር ትንታኔ፣

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን መነሻ ምክንያቶች ወስደን አጠር ያለ ትንታኔ ለመስጠት ያህል፣ የአፄ ቴዎድሮስ የአገራዊ ሠራዊት ምስረታ በታሪክ ትልቅ ስፍራ ያለውና ለመጪዎቹ ነገስታት ለዘመናዊ ሠራዊት ምስረታ ጥርጊያ መንገድ የከፈተ ቢሆንም ከፍላጎትና ጥረት አልፎ እንደሠራዊት ቀን ሊታሰብ የሚችል ፋይዳ ነበረው ማለት አይቻልም። የአድዋ ጦርነት ኢትዮጲያ ነፃነቷን ጠብቃ እንድትቆይ ያደረገ ብቻ ሳይሆን የመላው ጥቁር ህዝቦች የድል ቀን በመሆኑ ከማናቸውም ቀናት በላይ ፋይዳው የጎላ ነው፣ ይህ ቀንበመላው አገራችን ብሄራዊ በዓል ሆኖ እየተከበረ ያለ በመሆኑ የሠራዊት ቀን ብሎ መሰየሙ የቀኑን ፋይዳ አያጎላውም።

ከዘመናዊ ሠራዊት ምስረታ አንፃር በ1910 በአፄ ኃይለስላሴ የክብር ዘበኛ ጦርን የማቋቋም፣ ለሠራዊት ዶክትሪን ማዘጋጀት፣ የአየር ኃይልን የማደራጀት ጅማሮ፣ እንዲሁም የገነት ጦር ት/ቤት መከፈት ታላላቅ እርምጃዎች ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህን እርምጃዎች ለዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ ተያያዥ ሂደቶች አድርጎ ከመውሰድ ውጪ በተናጠል ወስዶ እንደሠራዊት ቀን ለማየት የሚያስቸግሩ ናቸው።

ከአምስት ዓመት ያልተቋረጠ የአርበኝነት ተጋድሎ በኋላ ጣሊያን ከኢትዮጲያ የተባረረበትና ሰንደቅ ዓላማችንም በአገራችን በገሀድ ዳግም የተውለበለበበት ቀን በመሆኑ፣ በተጨማሪም በዚህ የአርበኝነት ተጋድሎ ከሌሎች የኢትዮጲያ አርበኞች በተጨማሪ የሆለታ ጦር ት/ቤት ምሩቃንና ሰልጣኞች የሰሩት ገድል ሊታሰብ የሚገባው ነው፣ ነገር ግን ይህ በዓል ከሌሎች አገራት የነፃነት ቀን ጋር በማያያዝ የጣሊያንየአምስት ዓመት ቆይታ እንደሌሎች አገራት አምነን ተቀብለን ሳይሆን ባልተቋረጠ የአርበኝነት ትግልየቆየንበትን ሁኔታ በመሆኑ ቅኝ ከተገዙ አገራት እኩል ጣሊያንን አባረን ነፃነታችንን ያገኘንበት ነው በሚል በሠራዊት ቀንነት ማክበሩ ተገቢ አይሆንም።

ታህሳስ 15 ቀን 1944 ሠራዊቱ ይጠቀምበት የነበረውን የእንግሊዝ ማዕረግና ዩኒፎርም በመተው የራሱን የማዕረግ ምልክትና የደንብ ልብስ ወይም ዩኒፎርም

እንዲለበስ በደንብ መደንገጉ ከዚህ በፊት በቴዎድሮስም ሆነ በምኒሊክ ጊዜ ሠራዊቱ የራሱ የማዕረግ ስያሜዎችና የአለባበስ ስርዓትም እንደነበረው ሲታወስ ይህ እርምጃ የማሻሻያ ስራ እንጂ መሰረታዊ ለውጥ አይደለም ብሎ መውሰድ ይቻላል።

በሌላ በኩል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግንቦት 20 1950 በተወሰነ ውሳኔ የሠራዊት ቀን በዚህ ቀን እንዲከበርየተደረገበትን ሁኔታ ታሪክን ከማስቀጠል አንፃር ተገቢ ይሆን ነበር። ነገር ግን ቀኑ በወቅቱ ንጉሱን ሊገለብጡ ያሰቡ ለነበሩ የሠራዊቱ አመራሮች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በተጀመረ የሠራዊት ስፖርት ቀን ባጋጣሚ ተጋብዘው ተገኝተው ውሳኔውን በዛው እንዲወስኑ ሆነ እንጂ ቀኑ ታሪካዊ ዳራ ኖሮት አልነበረም።

የሶማሊያ ወረራ የተቀለበሰበት ሁኔታም የአገርን ሉዓላዊነት ለማስከበር የተደረገ ከፍተኛ የጀግንነት ተጋድሎ ነው። ይህ ጦርነት በወቅቱ የነበረው መንግስት በኤርትራ እና በሌሎችም ግንባሮች ተወጥሮ በጦርነት ላይ በነበረበት ሁኔታ የተካሄደ በመሆኑ ጦርነቱ የሠራዊታችን ታሪክ አንድ አካል ነበር ብሎ ማሰብ ይቻላል። በሌላ በኩል ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በአዋጅ የተቋቋመበትን ቀን ምክንያት በማድረግ ሠራዊታችን ሲያከብረው የነበረው የካቲት 7 ቀን የመከላከያ ሠራዊታችን ከ1988 ዓ.ም በፊት የነበረውን ታሪክ በሙሉ ዋጋ የሚያሳጣ ነው።

### ማጠቃለያ

በመሆኑም፣ ሁሉም ታሪኮቻችን የየራሳቸው ፋይዳ ቢኖራቸውም የኢትዮጲያ ሠራዊት እንደአንድ የአገሪቱ ተቋም ሆኖ

በሚኒስትር መስሪያ ቤትነት ደረጃ የተቋቋመበት ጥቅምት 15 ቀን 1900 ለሠራዊት ቀንነት ሚዛን የደፋ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ ቀን ሚኒሊክ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ማቋቋማቸውን ለዓለም አገራት ካሳወቁ[23] በኋላ ዜናውበአሜሪካና በእንግሊዝ ጋዜጦች ታትሞ ወጥቷል። ኒወዮርክ ታይምስ Cabinet for Menelik የአቢሲኒያው ንጉስ በአገራቸው የአውሮፓን ስርዓት አስተዋወቁ በሚል ርዕስ[24]፣ The Argus የተባለ የአውስትራሊያ ጋዜጣ ከለንደን Advancing with the time በሚል ርዕስ፣ እንዲሁም የእንግሊዙ Electric telegraph ከምፅዋ፣ እንዲሁም Daily News ከለንደን Reform in Abyssinia[25] በሚል ርዕስ አራቱም ጋዜጦች እ.ኤ.አ ኦክቶበር 29 ቀን 1907 ዓ.ም ዜናውን ዘግበውታል።

በመሆኑም የዛሬውን የመከላከያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን፣ በወቅቱ የጦር ሚኒስቴርን፣ ህጋዊና ኦፊሴላዊ በሆነ ሁኔታ፣ የዓለም መንግስታት ጭምር እንዲያውቁት ተደርጎ የተቋቋመበት ቀን፣ የሠራዊት ቀን ተደርጎ እንዲከበር ሲወሰን የሠራዊታችንንም ይሁን የአገራችንን ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን በማየት ታሪካዊ ዳራውን ጠብቀን ለትውልድ የምናሸጋግርበትና ተቋማዊ ቀጣይነቱን የምናረጋግጥበት የትውልድ ቅብብሎሽ ትውፊት አድርገን በመውሰድ ነው።

በዚሁ መሰረት የጦር ሚኒስቴር በህግ የተመሰረተበትን ቀን መሰረት አድርጎ የሚከበረው የመጀመሪያው የኢትዮጲያ መከላከያ ሠራዊት ቀን ጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ተከብሯል። ይህንን በዓል በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት በብሄራዊ ደረጃ በሚገባው መልኩ በድምቀት ለማክበር ባይቻልም ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በፎቶ አውደ-ርዕይና በፓናል ውይይት፣ በዕለቱ ጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ደግሞ "የእሳት ቀለበት - የሕግ ማስከበር ዘመቻ ንፍቀ-መዋዕል" በሚል ርዕስ የመጀመሪያውን ዙር የሕግ ማስከበርና ሉዓላዊነት ዘመቻ በተመለከተ በተዘጋጀ የመፅሃፍ ምረቃ ታስቦ እንዲውል ተደርጓል።

## ዋቢ መጽሐፍት


Beshir Ahmed. “Armed Forces Remembrance Day 2022 highlight: January 15 in Nigeria history – Explainer”. 15, January 2022. BBC News. https://www.bbc.com/pidgin/media-60009354, Accessed on 08, September 2023.

Department of Military Veterans. “President Jacob Zuma presides over Armed Forces Day celebration in Port Elizabeth, 21 Febraury”. 04, February 2016. http://www.dmv.gov.za/news/armed-forces-day.htm, Accessed on 29, August 2023.

Embassy of Romania in Bosnia and Herzegovina. “25 October - Romanian Armed Forces Day”, https://sarajevo.mae.ro/en/local-news/862, Accessed on 02, September 2023.

Ministry of Defense. “Indian Army celebrated its 74$^{th}$ Army Day”. PIB Delhi. 15, January 2022. https://pib.gov.in/ PressReleasePage. aspx?PRID=1790154,


[23] ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣ አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት፣ 1984፣ 360። (ጳውሎ ኞኞ የሚኒስትሮች ሹመትን ጥቅምት 14
አድርጎ ይወሰደዋል።)

[24] New York Times. “Cabinet for Menelik-Abyssinian King Introducing European Methods” 29, October 1907. https://www.nytimes.com/1907/10/29/archives/cabinet-for-menelik-abyssinian-king introducing-european- methods-in.html, Accessed on 07, August 2023.

[25] The Argus. “Reform in Abyssinia”. 29, October 1907. https://www.britishnewspaperarchive.co.uk/search/results/ 1907-10-29/1907-10-31?basicsearch=reform%20 in%20abyssinia&exactsearch=false&place=london%2c%20london%2c%20england&retrievecountrycounts=false&, Accessed on 07, August 2023.

Accessed on 01 September 2023.

Ministry of National Defense. “Polish Army Day 2022”. 27, July 2022. https://www.gov.pl/web/national-defence/polish-army-day-2022, Accessed on 02, September 2023.

National Today. “Egypt: Armed Forces Day – October 06, 2023”. 06, October 2023. https://nationaltoday.com/egypt-armed-forces-day/, Accessed on 08 October 2023.

New York Times. “Cabinet for Menelik-Abyssinian King Introducing European Methods” 29, October 1907. https://www.nytimes.com/1907/10/29/archives/cabinet-for-menelik-abyssinian-king introducing-european- methods-in.html, Accessed on 07, August 2023.

PAGASA. “The 80th Armed Forces of the Philippines Day”. Official Gezette. 21 December. 2015. https://www.officialgazette.gov.ph/2015/12/21/the-80th-afp-day/, Accessed on 01 September 2023.

Paolo Melissi. “4 November: Italian Unity and Armed Forces Day”. Italian Traditions. 04, November 2022. https://italian-traditions.com/4-november-italian-unity-armed-forces-day/, Accessed on 02, September 2023.

Paul B. Henze, Layers of Time – A History of Ethiopia. London: Palgrave. 2002.

The Argus. “Reform in Abyssinia”. 29, October 1907. https://www.britishnewspaperarchive.co.uk/search/results/ 1907-10-29/1907-10-31?basicsearch=reform%20 in%20abyssinia&exactsearch=false&place=london% 2c%20london% 2c%20england&retrievecountrycounts=false&, Accessed on 07, August 2023.

U.S. Government Publishing Office “Armed Forces Day”. 12, May 2020. https://www.govinfo.gov/features/armed-forces-day. Accessed on 01 September 2023.

ZD. China Focus: "Be ready to win wars," China's Xi orders reshaped PLA. Xinhua. 01, August 2017. http://www.xinhuanet.com// english/2017-08/01/c_136491455.htm, Accessed on 03 September 2023.

መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ- የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1999።

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ዝክረ ነገር፣ አዲስ አበባ፣ ነፃነት ማተሚያ ቤት፣ 1942።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ዐፄ ምኒልክ አና የኢትዮጲያ አንድነት፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጲያ ታሪክ - ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ አዲስ አበባ፣ 1936።

አበበ ወ/ተንሳይ፣ ቀ.ሠ ና ጦር ሠ.  አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ቤት፣ 2000።

ገስጥ ተጫኔ፣ የቀድሞው ጦር - 1927-1983፣ አዲስ አበባ፣ ዜድ.ኤ. ማተሚያ ቤት፣ 2006።

ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣ አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት፣ 1984።